# ይዘት

**ክፍል አንድ**

**1. መግቢያ**

**ክፍል ሁለት**

**2. የማኑዋሉ አስፈላጊነት**

2.1. ዋና ዓላማ

2.1.1. ዝርዝር ዓላማዎች

**ክፍል ሦስት**

**3. የድጋፍና ክትትል አሰጣጥ ሂደት**

3.1. የድጋፍ አሰጣጥ ዑደቶች

**ክፍል አራት**

4.የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ድጋፍ የሚሰጡባቸው መስኮች/ Areas of Support/

4.1. ለጤና ኬላዎች /ቀበሌዎች/ የሚሰጡት መደበኛ ድጋፍ

4.1.1 አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ መስጠት

4.1.2.በፕሮግራሞች አተገባበር ላይ ድጋፍ መስጠት

**4.1.2.1.** የጤና ልማት ሠራዊት ግንባታን ማጠናከር

**4.1.2.2.** የቤተሰብ ጤና አገልግሎት

**4.1.2.3.** በሽታ መከላከልና መቆጣጠርን በተመለከተ

**4.1.2.4.** ሀይጂንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ

የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በሚከተሉት ተግባራት ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡-

ክፍል አምስት

5. የስራ አፈጻጸም ግምገማ ማካሄድ/Review Meeting/

5.1. በጤና ጣቢያ ደረጃ የሚደረግ ወርሃዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ

6.አፈጻጸምን ማዕከል ያደረገ ዕውቅናና ማበረታቻ መስጠት

6.2. ጠንካራ ድጋፍና ክትትል ከሚሰጥ ጤና ጣቢያ የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶች

7. አባሪዎች

7.1. **የድጋፋዊ ክትትል ቼክሊስት.................................................................................................................**

**8. ድጋፍ** የሚሰጡ ባለሙያዎች ሊገነዘቧቸው የሚገቡ ማጣቀሻ መመሪያዎችና ማኑዋሎች

3
5
4
7
6
8
9
10
11
12
13
14
15
16
17
18
19
20
21
22
23
24
25
26
27
29
28
30
31

## ክፍል አንድ

# 1. መግቢያ

የጤና ፖሊሲያችን ማጠንጠኛ የሆነውን የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተደራሽና ውጤታማ ለማድረግ ላለፉት አስር ዓመታት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተቀርፆ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የአገራችን ዋና ዋና የጤና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችለውን ፕሮግራም አተገባበር ውጤታማና ብቃት ያለው ለማድረግ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተገቢ ድጋፍና የአቅም ግንባታ እንዲያገኙ ለማስቻል የጤና ጣቢያ - ጤና ኬላ ትስስር ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አንድ ጤና ጣቢያ በአማካይ ለ25,000 ህዝብና አንድ ጤና ኬላ ለ5,000 ህዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ ተደራጅቷል፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ ጤና ጣቢያ በስሩ ካሉ አምስት ጤና ኬላዎች ጋር እንደ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ/ዩኒት/ በመደራጀት ተደራሽነት ያለው መሠረታዊ የጤና አገልግሎት በጥራትና በፍትሀዊነት ለመስጠት የሚያስችል የትስስር አተገባበር መመሪያ ተዘጋጅቶለት ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል፡፡

የጤና ጣቢያና ጤና ኬላዎች ትስስር ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ትግበራና በጤና ጣቢያ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አዎንታዊ ለውጦች መታየት ጀምረዋል፡፡ ለአብነትም የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ወደ ቀበሌዎች እየወረዱ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን መደገፍ መጀመራቸው፤ በአብዛኛው አካባቢዎች በተቆራረጠ መልኩም ቢሆን የጋራ ዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና የስራ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ መጀመራቸው፤ ጤና ጣቢያዎች በስራቸው የሚገኙ ጤና ኬላዎችን በግብዓት እየደገፉ መሆኑ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ደረጃ ወጥ የሆነና ችግር ፈቺ የድጋፍ፣ የክትትልና የስራ አፈፃፀም ግምገማ ባለመተግበራቸው ለውጦቹ ከቦታ ቦታ የተለያዩ መሆናቸው በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ የመስክ ምልከታዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህንም ልዩነቶች ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ስራዎችን የመተግበርና የመምራት የአቅም ልዩነቶች እንደሚመነጩም ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድን የበለጠ ለማጠናከርና ከቦታ ቦታ የሚታዩትን የድጋፍና ክትትል እንዲሁም የስራ አፈፃፀም ግምገማዎች ችግር ፈቺና ውጤታማ በሆነ

መልኩ ለማከናወን ይረዳ ዘንድ ይህ ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል ሁለት
# 2. የማኑዋሉ አስፈላጊነት

የጤና ጣቢያ እና የጤና ኬላ ትስስር ተቋማቱ ለተሻለ ውጤት በአንድ ዓላማ ዙሪያ አንድ እቅድ ይዘው ለጋራ አፈፃፀም እንዲንቀሳቀሱ ማስቻል መሆኑ በትስስር መመሪያው ላይ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ዓላማውም ጤና ጣቢያና በስሩ የሚገኙ ጤና ኬላዎች እንደ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት መስጫ አሃድ/ዩኒት በመተሳሰር ለህብረተሰቡ ጥራት ያለው ጤናን የማበልፀግ፣ በሽታን የመከላከልና መሰረታዊ የሆኑ የህክምና አገልግሎቶች ለማቅረብ ነው፡፡ በተጨማሪም ጤና ጣቢያው በጤና ኬላ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን አቅም በመገንባት፣ ያልተቆራረጠ የግብዓት አቅርቦት በማረጋገጥ እንዲሁም የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ በማጠናከር የሚጠበቅበትን ድርሻ እንዲወጣ ለማስቻል ነው፡፡

የትስስሩ መመሪያ ተግባራዊ ከሆነ በኂላ በሁለቱም ተቋማት የነበረውን አለመደጋገፍና ተቀናጅቶ ያለመስራት ችግር እንዲቀረፍና እንደ አንድ አሃድ እንዲሰሩ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በሴክተሩ በየዓመቱ የሚከናወኑ የተቀናጀ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም ኢንስፔክሽን ስራዎች እንደሚያሳዩት የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ወደ ጤና ኬላና በየጎጡ ወርደው ሙያዊ ድጋፍ በሚሰጡበት ጊዜ ምን እንደሚደግፉ፣ እንዴት እንደሚደግፉ፣ ድጋፋቸው በምን እንደሚለካና ችግር ፈቺ የሆነ ዝርዝር ቼክ-ሊስት ያልተካተተበት መሆኑ ተለይቷል፡፡ በስራቸው በሚገኙ ጤና ኬላዎች መካከል የሚደረገው መደጋገፍና ክትትል ወጥነት እንዲኖረው እንዲሁም በየወሩ በጤና ጣቢያዎች ደረጃ የሚካሄዱ የስራ አፈፃፀም ግምገማዎች በምን አግባብ መከናወን እንዳለባቸውና ከግምገማው በኂላ የግምገማውን ግኝቶች ስራዎችን ለማሻሻል በምን መልኩ መጠቀም እንዳለባቸው አቅጣጫ ለማስቀመጥ እንዲቻል ይህንን ማንዋል ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 2.1. ዋና ዓላማ

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን ስራን የመፈፀምና የመምራት ብቃት እንዲሁም ተነሳሽነት በማሳደግና ምቹ የስራ አካባቢ በመፍጠር ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ለሕብረተሰቡ ማድረስ የሚችሉበት ደረጃ ማድረስ ነው፡፡

## 2.1.1. ዝርዝር ዓላማዎች

☛የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ስራን የማቀድ፣ የመተግበር፣ የመገምገም እና መረጃን ለውሳኔ የመጠቀም ክህሎታቸውን ለማሳደግ፣

☛የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በተቀመጡ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች መሠረት እንዲሰሩና በቂ የግብአት አቅርቦት እንዲሟላላቸው በማድረግ ጥራቱ የተጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ ለመደገፍ፣

☛የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አዳዲስ ስለሚወጡ መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና መረጃዎች ድጋፍ በሚሰጥዋቸው የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ፣

☛የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሚደርሱባቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች በየደረጃው የሚቀረፉበት ሁኔታ በመፍጠር ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር ለማድረግ፣

☛ጤና ጣቢያዎች ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የሚሰጡትን ድጋፍ በመረጃ የተደገፈና ወጥነት ያለው ለማድረግ፤

# ክፍል ሦስት

# የ3. ድጋፍና ክትትል አሰጣጥ

በጤናው ሴክተር ድጋፋዊ ክትትል ማለት በየደረጃው በጤና ስርዓቱ ውስጥ መቀራረብና አብሮ የመስራት ባህል፣ ችግሮችን ነቅሶ የማውጣትና መፍትሔ ማበጀትን እንዲሁም በስታንዳርድ መሠረት መስራትን በማጠናከር የጤና አገልግሎት ጥራቱ እንዲጎለብት የሚያስችል አንድ ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሚያደርጉትን ድጋፍ  ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር በመሆን የሁኔታ ትንተና በማድረግ መለየትና ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ የድጋፍ አሰጣጥ ሂደቱ ከእቅድ ጀምሮ እስከ የማጠቃለያ ምዕራፍ ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚከናወን ነው፡፡ በዚህም መሠረት የጤና ጣቢያዎች ለጤና

ኬላዎች/ቀበሌዎች የሚሰጡት ድጋፍና ክትትል ከዚህ በታች በተቀመጡት ሶስት አግባቦች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ እነዚህም፡-

ሀ. መደበኛ የመስክ ድጋፍ መስጠት፣

ለ. ወርሃዊ የአፈፃፀም ግምገማ/Review Meeting/ ማካሄድ፣

ሐ. አፈፃፀምን መሠረት ያደረገ እውቅናና ማበረታቻ መስጠት ናቸው፡፡

በዚህ ማንዋል መደበኛ የመስክ ድጋፍ ማለት በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትግበራ ላይ መሰራት ያለባቸውን ቁልፍ ተግባራት በመለየት የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በቀበሌዎች/ጤና ኬላዎች በመደበኛነት በአካል በመገኘት ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሚሰጡት ሙያዊ እገዛ ሲሆን በማብቃት (mentoring)፣ ገንቢ ግብረ-መልስ በመስጠት፣ ችግሮችን በጋራ መፍታት ላይ የሚያተኩር እና በድጋፍ ሰጪ እና ድጋፍ ተቀባይ መካከል የሁለትዮሽ ተግባቦት /two-way communication/ እንዲኖር በማድረግ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን ብቃት ለመገንባት አይነተኛ ሚና የሚጫወት ስልት ነው፡፡ ይኸውም የጤና አገልግሎት ጥራት፣ ተደራሽነትና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል፡፡

ወርሀዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና አፈፃፀምን መሠረት ያደረገ እውቅናና ማበረታቻ መስጠት ሌሎች የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን የስራ አፈፃፀም አቅም ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚጫወቱ ሲሆን ዝርዝር አተገባበራቸው በዚህ ሰነድ ራሳቸውን ችለው በክፍል ቀርበዋል፡፡

ከጤና ጣቢያ ወደ ጤና ኬላ ለድጋፍ የሚሰማሩ ጤና ባለሙያዎች ውጤታማ ድጋፍ እንዲሰጡ ሊኖሯቸው የሚገቡ መልካም እሴቶችና ባህሪያት ማዳበርና ልማዳዊ የተቆጣጣሪነት ባህርያትን በጊዜ ሂደት ማስወገድ ይገባቸዋል፡፡ እነዚህ መልካም ባህሪያት በጤና ባለሙያዎችና በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች መካከል መልካም የስራ ግንኙነትን በመፍጠር፣ የአብሮነት ስሜትና የባለቤትነት መንፈስ በማሳደግ ውጤታማ ድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት ለመዘርጋት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የቁጥጥር መሰል ድጋፍ አሰጣጥ ባህሪያት በድጋፍ ሰጪውና ተቀባዩ መካከል ያለመተማመንን የሚፈጥር፣ ሞራል የሚነካና አሰልቺ እንዲሁም የሚፈለገውን ውጤትም አያስገኝም፡፡

## ሠንጠረዥ 1 ፡- መልካም/ችግር ፈቺ/ ድጋፍ አሰጣጥ እንዲሁም የተቆጣጣሪነት ባህሪያት በንፅፅር የሚያሳይ

| ችግር ፈቺ/መልካም/ የድጋፍ አሰጣጥ ባህሪያት | የተቆጣጣሪነት ባህሪያት |
|---|---|
| ♣የባለሙያዎችን የማስፈፀም አቅም እንዲሻሻልና መልካም የስራ ግንኙነት በመፍጠር ላይ ያተኩራል፤<br>♣የድጋፍ አሰጣጡ ሂደት የአስተማሪነት፣ የአሰልጣኝነት (coach) እንዲሁም ሜንተርሺፕን የተከተለ ነው፤<br>♣ከባቢያዊ መረጃዎችን ለአፈፃፀም ግምገማና ማነቆዎችን ለመፍታት ይጠቀማል፤<br>♣ስራዎችን ባልተቆራረጠ መልኩ/regularly/ ክትትል ያደርጋል/ታደርጋለች፤<br>♣ገንቢ ድጋፍ ብቻ ይሰጣል፤ | ♣የባለሙያዎችን ስህተቶች በማውጣት ላይ ያተኩራል፤<br>♣ድጋፍ ሰጪው ባለሙያ ራሱን እንደፖሊስ ያያል፤<br>♣አልፎ አልፎ /በተቆራረጠ/ ችግር ለመፍታት ይሞክራል /ትሞክራለች፤<br>♣አነስተኛ ወይም የተቆራረጠ ክትትል ያደርጋል /ታደርጋለች፤<br>♣ጥፋተኞችን መቅጣት ላይ ያተኩራል፤ |

## ለድጋፍ የሚሰማራ ባለሙያ ሊላበሳቸው የሚገቡ እሴቶች

♣አዳማጭነት
♣አክባሪነት፣
♣ችግር ፈቺነት/መፍትሔ ተኮርነት/
♣የራስን ክፍተት መረዳት
♣በመማማር ማመን
♣በቡድን መስራት
♣የማህበረሰብ ባለቤትነት ማጎልበት

## 3.1. የድጋፍ አሰጣጥ ዑደት

**በዚህ ርዕስ ስር የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ወደ ጤና ኬላ ለድጋፍ በሚሰማሩበት ወቅት ሊከተሉት የሚገባ የድጋፍ አሰጣጥ ዑደት በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡-**

### 3.1.1. የድጋፍ አሰጣጥ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ

#### 3.1.1.1. የጤና ጣቢያ ባለሙያዎችን ለድጋፍ ማዘጋጀት፣ ኦሬንቴሽን/ስልጠና መስጠት

የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በቅድሚያ ስለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙና የሚሰጡ አገልግሎቶች ይዘት፣ የትና እንዴት እንደሚተገበሩ እንዲሁም የድጋፍ አሰጣጥ ስልቶች ላይ በቂ የሆነ ግንዛቤና ክህሎት እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸውም በጤና ጣቢያ ዳይሬክተር አስተባባሪነት በሚከናወን ኦሬንቴሽን/ስልጠና ይተገበራል፡፡ ኦረንቴሽኑን ለመስጠት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

- በጤና ጣቢያ ደረጃ በየፕሮግራሙ ስልጠና የወሰዱና የተሻለ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ለይቶ ለኦረንቴሽኑ በአመቻችነት መጠቀም፣
- የድጋፍ አሰጣጥ ክህሎትን ለማሻሻል የተዘጋጀውን ይህንን ማንዋል ተጠቅሞ ድጋፋዊ ክትትል አሰጣጥ ዑደት፣ ዘዴዎች እና አሳታፊነት ላይ ማሰልጠን፤
- ኦረንቴሽኑን ቢያንስ በየአመቱ የዝግጅት ምዕራፍ ወቅት አዲስና ነባር ደጋፊ ባለሙያዎችን በማሳተፍ መስጠት፣

#### 3.1.1.2. ለድጋፍና ክትትል ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት

ድጋፍ የሚሰጡ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎችን ከማሰልጠን ባሻገር ውጤታማ ድጋፍ አሰጣጥ እንዲኖር የሚያግዙ ቁሳቁሶች ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም ፡-

- ደረጃውን የጠበቀ የድጋፍና ክትትል ቼክሊስት፣
- አጋዥ ማንዋሎችንና መርጃ መፃህፍቶችን፣ ትራንስፖርትና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ግብአቶችን እንዲሟሉ ማድረግ ናቸው፡፡

## ሀ. የድጋፍና ክትትል ቼክሊስት ማዘጋጀት

የድጋፍና ክትትል ቼክሊስት ሲባል ድጋፍ የሚሰጠው የጤና ጣቢያ ባለሙያ ቅድሚያ ሰጥቶ የሚደግፋቸው፣ የሚከታተላቸውና የሚመዘግባቸውን ጉዳዮች በዝርዝር የያዘ ሰነድ ነው፡፡ መነሻ ሊሆን የሚችል ናሙና ቼክሊስት ከዚህ ማንዋል ጋር አባሪ ተደርጓል፤ ነገር ግን ጤና ጣቢያዎች እንደየአካባቢያቸው ትኩረት በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን ቼክሊስት ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡ ቼክሊስቱ ባለሙያው ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር እንዲደግፍና መረጃዎችን እንዲመዘግብ ያግዘዋል፡፡ ባለሙያዎቹ የሚመዘግቧቸውን መረጃዎች በድጋፋዊ ክትትል ወቅት ምን አይነት የማስተካከያ ድጋፍ መውሰድ እንዳለባቸውና በአጭር (Quick win)፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ ሊፈቱ የሚችሉና ክትትል የሚያስፈልጋቸው ተግባራትን መለየት እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡

### ለ. አጋዥ ማንዋሎችና መርጃ መፃህፍቶች ማሟላት

ለድጋፍና ክትትል ወደ ቀበሌዎች የሚሰማሩ የጤና ጣበያ ባለሙያዎች በማጣቀሻነት የሚገለገሉባቸው መመሪያዎችና ማንዋሎች ሊሟላላቸውና ባለሙያዎቹም አስፈላጊ ዝግጅት ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ለዚህ ስራ አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የተለዩ መመሪያዎችና ማንዋሎች በናሙናነት ከዚህ ማንዋል ጋር በአባሪ 9 ተካትተዋል፡፡

በተጨማሪም ድጋፋዊ የመስክ ጉብኝት ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ግብአቶች ለምሳሌ የትራንስፖርት አቅርቦት እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ አስቀድሞ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

**የተሻሻለ የስራ አፈፃፀም**

## የድጋፍና ክትትል ቼክሊስት ሊያካትታቸው የሚገቡ ነጥቦች/ Checklist preparation Frame Work/

1. በጤና ኬላው እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶችን ለማወቅ የሚያስችሉ ነጥቦች
2. በጤና ኬላው እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶች ጥራት/ተገቢነት/ ለማወቅ

3. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት/ Plan vs Achievement wall chart or report/ ለመፈተሸ፤
4. በዚህ ማንዋል በክፍል አራት የተዘረዘሩት የድጋፍ መስኮችን ወዘተ ታሳቢ ያደረገ የድጋፍ እና ክትትል ቼክሊስት መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

### 3.1.1.2. ተከታታይ ድጋፋዊ ክትትል ለማካሄድ ማቀድ

ጤና ጣቢያዎች ለጤና ኬላዎች የሚያደርጉትን ድጋፍና ክትትል የአመት ወይም የሩብ ዓመት እቅዳቸው አካል አድርገው ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ ለድጋፍና ክትትል በሚታቀድበት ወቅት የተለያዩ መረጃዎችን (ለምሳሌ፡- የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የድጋፍና ክትትል ሪፖርቶች.ወዘተ) በመተንተን የጤና ኬላዎችን በአፈፃፀም ደረጃቸው በከፍተኛ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ መድቦ እንደየፍላጎታቸው ለመደገፍ ማቀድ አስፈላጊ ነው፡፡ ማለትም ዝቅተኛ አፈፃፀም ላላቸው ጤና ኬላዎች በአንፃራዊነት ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ለመስጠት ማቀድ፡፡ በዕቅዱም ወቅት የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች መሳተፍ አለባቸው፡፡ በአጠቃላይ ዕቅዱ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

- ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ፓኬጆችን በመለየት ድጋፉ የትና እንዴት ለመስጠት እንደታሰበ ማስቀመጥ (በጤና ኬላ በፕሮግራሞች ዙሪያ፣ በማህበረሰብ ደረጃ፣ ወዘተ.)፣
- ድጋፉ መቼ ለመስጠት እንደታቀደ፣
- በድጋፉ ማሳካት የታሰቡትን ዓላማዎች ምን እንደሆኑ፣
- የድጋፍና ክትትሉ ስኬት መለኪያዎች

### ሀ. ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ፓኬጆችን በመለየት ድጋፉ የትና እንዴት ለመስጠት እንደታሰበ ማስቀመጥ

- ቅድሚያ ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮችን መለየትና በእነዚህ ላይ ተከታታይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ትኩረት የሚሹ የድጋፍ መስኮች ለመለየት የሚከተሉትን በመነሻነት መውሰድ ይቻላል፡-
- ዝቅተኛ ሽፋን ባላቸው ፕሮግራሞች/ፓኬጆች፣
- ቀድሞ በተደረገው ድጋፋዊ ክትትል ወቅት በቂ ድጋፍ ያልተደረገባቸው መስኮች፣
- ቀድሞ በተደረገው ድጋፋዊ ክትትል ወቅት የተገኙ ያልተሟሉ ሪፖርቶች ካሉ፣
- ሌሎች በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ወይም በህብረተሰቡ የሚነሱ ችግሮች ካሉ ወዘተ.

## ለ. ድጋፋዊ ክትትሉ መቼ ማካሄድ እንደታሰበ ማስቀመጥ

ድጋፍ የሚደረግባቸው መስኮች ከተለዩ በኋላ የድጋፋዊ ክትትሉ የጊዜ ሰሌዳ መዘጋጀት አለበት፡፡ ስለሆነም፡-

☛ድጋፍ የሚደረግላቸው ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የተዘጋጀውን የጊዜ ሰሌዳ እንዲያውቁት ማድረግ አስፈላጊ ነው፤

☛የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ለድጋፍ በሚሰማሩበት ወቅት በቂ የድጋፍ ጊዜ መመደብ አለባቸው፣ የስራ ላይ ስልጠና/ሜንተርሺፕ እስከመስጠት የሚያስችል ጊዜ መመደብ ይኖርባቸዋል፤

☛በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ድጋፍ መስጠት፤

## 3.1.2. ድጋፋዊ ክትትል ማካሄድ

የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ወደ ቀበሌ ተሰማርተው በሚደግፉበት ጊዜ የሚከተሉትን ተግባራት መከወን አለባቸው፡-

ሀ) መረጃን መሰብሰብ

ለ) ችግርን መፍታት /Problem-solving/

ሐ) ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት/ and constructive feedback/

መ) የድጋፉ ግኝቶች በአግባቡ መመዝገብ

## ሀ. መረጃ መሰብሰብ

☛የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የሚከተሉትን መንገዶችን በመከተል መረጃ መሰብሰብ አለባቸው፡-

የጤና ኬላውን ግቢ በመመልከት፣

☛ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን በማወያየት አፈጻፀማቸውንና ተግዳሮቶቻቸውን መለየት፤

☛የጤና ኬላ መዛግብትንና የሴቶች ልማት ቡድን ሪፖርቶችን በመፈተሽ፤

☛ቼክሊስቱን በመጠቀም ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ ከቀበሌ አመራሮች፣ ከቤተሰቦችና ከልማት ቡድን መሪዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ፤

☛ከቀድሞ ድጋፋዊ ጉብኝት የአስተያየት መስጫ መዝገብ በመመልከት

## ለ. ማነቆዎችን መፍታት/Problem-solving/

የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ድጋፍና ክትትል በሚሰጡበት ወቅት የሚያስተውሏቸው ክፍተቶች ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ወይም ከልማት ቡድን መሪዎች ጋር በጋራ ችግሮችን መፍታት ይኖርባቸዋል፡፡ ችግሮቹን ለመፍታትም የሚከተሉትን ቅደም ተከተል ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡-

## ተግባር 1: ችግሩና ያስከተለው ተፅእኖ ማብራራት

☛በችግሩ፣ በችግሮቹ መንስኤዎችና በአሰራር ሂደቶች ላይ እንጂ በግለሰቦች ላይ አለማተኮር

☛የማነቆውን የአጭርና የረዥም ጊዜ ተፅእኖ ምን እንደሆነ ማብራራት፤

☛በአንድ ጊዜ አንድ ማነቆ ወይም የተወሰኑ ማነቆዎችን በተለይም ከፍተኛ ተፅዕኖ ያለውን በቅድሚያ ለመፍታት ለይቶ ማስቀመጥ፣

☛የተለየውን ማነቆ ግልፅ በሆነ መልኩ ማብራራት እንዲሁም በመረጃ ማስደገፍ ያስፈልጋል፤

## ተግባር 2: የማነቆዎቹ ምንጭ ላይ መወያየት

☛የማነቆውን ምንጭ ለመለየት በተደጋጋሚ አምስት ጊዜ "ለምን" ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል (ይህንን በስዕላዊ መግለጫ 1 በተቀመጠው መሠረት መስራት)

☛"ለምን" እያሉ መጠየቅ ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን ብቻ ለመውቀስ እንደ አጋጣሚ መወሰድ የለበትም ይልቁንም የማነቆው ምንጭ ከሌሎች ጉዳዮች አንፃርም ማየት አስፈላጊ ነው (ለምሳሌ ከማህበረሰቡ አካላት፣ ከመረጃ ክፍተት ወዘተ.)፤

☛ከተለዩት ምንጮች መካከል በቀላሉ መፍታት ከሚቻለው መጀመር ያስፈልጋል፤

**ለምሳሌ፡-** በአንድ ጤና ኬላ ወርሃዊ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ለ80 ሴቶች ለመስጠት ታቅዶ አገልግሎቱን ያገኙት ግን 15 ብቻ ቢሆኑ ከጤና ጣቢያ ድጋፍ የሚሰጥ ባለሙያ ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር በመሆን ለዚህ ዝቅተኛ አፈጻጸም መከሰት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን ከታች ባለው ስዕላዊ መግለጫ እንደተገለፀው በመተንተን የመፍትሄ ስልቶችን መንደፍና ለተፈጻሚነታቸዉ በጋራ በመስራት ችግር ፈቺ የሆነ ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል፡፡

ከላይ በስዕላዊ መግለጫው የተመለከተው ምሳሌ በሌሎችም የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች አፈጻጸም የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ለይቶ ለመፍታት እንደማሳያ የቀረበ ነው፡፡ ይህ ዘዴ the five “WHY” method የሚባልና የአንድ ችግር ስርወ ምንጭ ለማወቅ/root cause analysis/ እና ምንጩን ለማድረቅ የሚያግዝ ሳይንሳዊ ዘዴ ነው፡፡ ስለሆነም ችግሩን ከሁሉም አቅጣጫ በመመልከት ትክክለኛውን ጥያቄ መጠየቅና ስርወ-ምንጭ ለማስቀመጥ መትጋት የእያንዳንዱ ድጋፍና ክትትል የሚሰጥ የጤና ጣቢያ ባለሙያና የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሀላፊነት ነው፡፡ ይህንን ዘዴ ከተከተልን እያንዳንዱን ስርወ-ምንጭ ለማድረቅ የሚረዱ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልቶችን ለመተለም እና ችግሩን ለመፍታት የሚረዱ አጋር አካላትን ለመለየት ያስችለናል፡፡

## ተግባር 3: መፍትሔዎችን ማስቀመጥ፣ መተግበርና በየጊዜው መለካት

☛የተመረጡትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ ተግባራትን መለየት፣

☛ወዲያውኑ መሰራት የሚችሉትን ተግባራት መጀመሪያ መስራት፤

☛የሚከናወኑትን ተግባራት፣ እንዴት ለመስራት፣ በማን እና መቼ ለማከናወን እንደታቀደ በሚያሳይ መልኩ የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት እና መተግበር፣

☛ለውጦችን መከታተልና መለካት፤

## ሐ. ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት

የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን በሚደግፉበት ወቅት ገንቢ የሆነ ግብረመልስ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ መረጃን የማሰባሰብ ስራው እንደተጠናቀቀ ድጋፍ የሚሰጠው ባለሙያ ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር በጋራ በመሆን ክፍተት ያለባቸውን ጉዳዮች በዝርዝር መለየትና ገንቢ የሆነ ግብረመልስ መስጠት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በአፈፃፀም ላይ ለተገኙ ክፍተቶች ግብረመልስ በሚሰጥበት ጊዜ ከጠንካራ ጎን በመጀመር፣ ስኬቶቻቸውን በማወደስ፣ መፍትሔ አመንጪ በመሆን እና  በዋና ዋና ድክመቶች ላይ በማተኮር መደገፍ ያስፈልጋል፡፡

## መ. የድጋዊ ክትትሉ ግኝቶችን ና የመፍትሔ አቅጣጫዎች በጤና ኬላ መዝገብ ማኖር

በጤና ኬላ ደረጃ የድጋፋዊ ጉብኝቱ ግኝቶች የሚመዘገቡበት መዝገብ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መዝገብ በእያንዳንዱ ጉብኝት ማጠቃለያ ድጋፍ የተሰጠበት ቀን፣ በምልከታው የተገኙ ግኝቶች፣ በቦታው የተሰጡ ድጋፎች/ሜንተርሺፕ/ እንዲሁም ስምምነት ላይ የተደረሰባቸው የቀጣይ የድርጊት መርሀ ግብሮች/ agreed action plans/ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡ የመዝገቡ ቅፅ በሠንጠረዥ (2) በተቀመጠው መልኩ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡

## 3.2. ድህረ ድጋፍ ክትትል ማድረግ

ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ ብቻ በራሱ ውጤታማ ሊሆን አይችልም፣ ድጋፍ በተደረገባቸውና በቀጣይ እንዲሰሩ ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮችን ክትትል ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡

### 3.2.1. የድጋፋዊ ክትትል ሪፖርት ማዘጋጀትና መገምገም

ከእያንዳንዱ ድጋፋዊ ክትትል መልስ ድጋፍ የሰጡ ባለሙያዎች በሰጡት ድጋፍ ዙሪያ የተሟላ ሪፖርት ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ይህ ሪፖርት የተገኙት ክፍተቶችን ለማረም የሚያስችሉ ተግባራት ለማቀድና በቀጣይ ለሚኖረው ድጋፋዊ ክትትል በመነሻነት ያገለግላል። በመሆኑም ሪፖርቱ በሠንጠረዥ (3) ነጥቦች በማካተት ተዘጋጅቶ ለጤና ጣቢያው ዳይሬክተር ወይም ለትስስር መሪ ማቅረብ ይገባቸዋል።

ከድጋፍና ክትትል በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ዳይሬክተርና የጤና ኤክስቴንሽን መርኃ-ግብር አስተባባሪ በየቀበሌው ከተመደቡ ባለሙያዎች ጋር አጠቃላይ ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል። በውይይቱ ጊዜ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡-

☛ምን አበረታች ስራዎች ታይተዋል?

☛ምን ምን አይነት ድጋፎች ተሰጥተዋል?

ምን ምን ክፍተቶች ነበሩ? የክፍተቶቹ ምንጭ?

☛እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት ምን ምን ስራዎች ታቅዷል?

☛ከጤና ጣቢያው ምን ይጠበቃል?

☛ወደ ሌሎች ቀበሌዎች/ልማት ቡድኖች ሊሰፉ የሚችሉ ምን ምርጥ ተሞክሮዎች ተለዩ?

የዚህን ውይይትና በቼክሊስት የተገኙትን መረጃዎች በማጠናቀር ለሚቀጥለው ወርሃዊ ግምገማ እንደግብአት መጠቀምና የተለዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስፋት ያስፈልጋል።

በድጋፋዊ ክትትል ጊዜ ጥሩ አፈጻጸም የሌላቸው ቀበሌዎች ተለይተው የችግሩ ምንጭ የድጋፍ አሰጣጡ ሁኔታ ደካማ መሆን የሚል ሆኖ ከተረጋገጠ በጥንካሬያቸው የተሻሉ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎችን በመመደብ እንዲደግፏቸው ማድረግ ያስፈልጋል።

መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ

☛ወንዶችን ያሳተፈ የቤተሰብ እቅድ ትምህርት መስጠት ፡

☛የደህረ ወሊድ ትምህርት በመስጠት

☛የወንዶችን የልማት ቡድን መጠቀም

☛ሞዴል ወንዶችን በመጠቀም ሌሎችን ማስተማር

…

የሴቶች ውሳኔ ሰጪነት

ለምን?

ለምን?

ለምን?

ለምን?

የባሎች ተጽእኖ

ልጅ ሃብት ነው ብሎ ማሰብማሰብማሰብ

የግንዛቤ እጥረት

የሚሰጠው የቤተሰብ እቅድ ትምህርት ወንዶችን ያሳተፈ ያለመሆን

…

…

….

የክህሎት ክፍተት

የግብዓት እጥረት

የሀይማኖት ተጽእኖ

# **ስዕል 1፡-** ዝቅተኛ የቤተሰብ እቅድ አፈጻጸም

## 3.2.2. የድርጊት መርሀ ግብሩን አፈፃፀም መከታተል

እያንዳንዱ ጤና ጣቢያ በባለሙያዎች የቀረቡለትን የድርጊት መርሀ ግብሮች አፈፃፀም መከታተልና ማገዝ አለበት፡፡ ከነዚህም የሚከተሉትን መከታተል አስፈላጊ ነው፡-

☛የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ለመስራት የተስማሙባቸው ጉዳዮችን ማከናወናቸውን፣

☛ከሚመለከታቸው የበላይ አካላት ጋር በመሆን ለጤና ኬላዎች የሚያስፈልጉ ግብአቶችና መድሀኒቶች አቅርቦት ችግር መፍታት፣

☛ወርሀዊ ርፖርቶችን መገምገም እንዲሁም ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር ባልተቆራረጠ መልኩ የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር የተሰጧቸው ግብረመልሶችን ስለመተግበራቸው

መከታተል፣

☛የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሚያጋጥሟቸው የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈቱ ማድረግ፣(ለምሳሌ፡- የሚገባቸው የትምህርት እድገት ያለማግኘት ቅሬታዎች ካሉ መለየትና እንዲፈቱ መጣር)፤

☛ከዚህ በፊት የተለዩ ችግሮች መስተካከላቸውን ማረጋገጥ፤

## ሠንጠረዥ 2. ለጤና ኬላ የሚሰጡ የድጋፍና ክትትል ተግባራት መዝገብ

ቀን:-----------------------------------------

ቀበሌ:--------------------------------------

የተደገፌው ጤና ኬላ......

**1. የተለዩ ክፍተቶች፣ የድጋፍ ክትትል እቅድ**

**3. የተለዩ ምርጥ ተሞክሮዎች፡-** ________________________________________________

________________________________________________________________

ደጋፊ ባለሙያ ስም -------------ሙያ------- ፊርማ:______________

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ 1፣ ------------- 2፣-----------------------------

| ተቁ | በቀበሌው የተደረገ የድጋፍና ክትትል ተግባራት | የተለዩ ክፍተቶች | የመፍትሄ ሃሳቦች | በማን ይከናወናል? | መቼ ይከናወናል? |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | |
| 2 | | | | | |
| 3 | | | | | |
| 4 | | | | | |

## ሠንጠረዥ.3. የጤና ኬላ ድጋፍ ሰጪ ባላሙያ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ

ቀን:------------------------------------------

የተደገፌው ቀበሌ:--------------------------------------

**1. የተለዩ ክፍተቶች፣ የድጋፍና ክትትል እቅድ**

2. የተለዩ ምርጥ ተሞክሮዎች፡- ________________________________________________
______________________________________________________________________________
____________________________________________

3. ድጋፍ የሰጠው ባለሙያ
   ስም............... ፊርማ............

| ተቁ | በቀበሌው የተደረጉ ድጋፍና ክትትል ተግባራት | የተለዩ ክፍተቶች | የመፍትሄ ሃሳቦች | በማን ይከናወናል? | መቼ ይከናወናል? | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | |
| 2 | | | | | | |
| 3 | | | | | | |
| 4 | | | | | | |

# ክፍል አራት

## 4.የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ድጋፍ የሚሰጡባቸው መስኮች/ Areas of Support/

### 4.1. ለጤና ኬላዎች /ቀበሌዎች/ የሚሰጡት መደበኛ ድጋፍ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በጤና ጣቢያቸው ትስስር ስር የሚገኙ ጤና ኬላዎችን መደበኛ ድጋፍ የሚሰጡባቸው መስኮች ናቸው፡፡ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ቀበሌዎችን ተከፋፍለው በየሙያ ዘርፋቸው መደገፍ የሚችሉ ሲሆን እንደ ሚድ ዋይፍ፣ የፋርማሲ ባለሙያና የጤና መረጃ ስርዓት ባለሙያ /HIT/ የመሳሰሉት ባለሙያዎች ግን የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶላቸው ለሁሉም ጤና ኬላዎች ድጋፍ እንዲሰጡ ተመቻችቶላቸው የድጋፍ ምልልሳቸውም በመደበኛነት ድጋፍ ከሚያደርጉት

ባለሙያዎች ያነሰ ይሆናል፡፡

የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ድጋፍና ክትትል በሚያደርጉበት ወቅት በቼክሊስት የሚታገዝ ሲሆን ድጋፍ የሚደረግባቸው ዋና ዋና ተግባራትም አስተዳደራዊና ፕሮግራሞች በሚል ተከፍለው በሚከተለው አግባብ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

## 4.1.1 አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ መስጠት

## ሀ. የዕቅድ ዝግጅት

ወረዳን መሰረት ያደረገ ዓመታዊ ዕቅድ ሲዘጋጅ በጤና ጣቢያው ስር ያሉ ጤና ኬላዎችን ባሳተፈ መልኩ ከወረዳ የሚሰጠውን ዕቅድ እንደመነሻ በመያዝ የቀበሌያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ /የቀበሌውን የህዝብ ብዛት፣ የሚጠበቁ ነፍሰጡር እናቶች፣ ለቤተሰብ ዕቅድ ታላሚ የሆኑ፣ ለክትባት ታላሚ የሆኑ ሴቶች እና ህፃናት ብዛት ወዘተ…/ ያገናዘበ የጤና ዕቅድ በጋራ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ዕቅዱ ከተዘጋጀ በኋላ ሁሉንም የጤና ጣቢያውን ባለሙያዎች እና የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን ባሳተፈ መልኩ የእቅድ ኦሬንቴሽን/ገለጻ በመስጠት፣የጋራ መግባባት በመፍጠር የውል ስምምነት በመፈራረም ተግባራዊነቱን መከታተል እና አፈጻጸሙን መገምገም ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በእቅድ ዝግጅት ወቅት ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሚከተሉት ተግባራት ላይ ድጋፍ ያደርጋሉ፡-

☛የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ የቀበሌ አመራሮችና የልማት ቡድን መሪዎችን ባሳተፈ መልኩ ከጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ጋር የተጣጣመ የቀበሌ ዓመታዊ፣ የስድሰት ወር፣ የሩብ ዓመትና የወር እቅድ እንዲዘጋጅ ያደርጋሉ፤

☛የጤና ፕሮግራሞች ዒላማ/Target/ እና ዒላማዎችን ለማሳካት መከናወን ያለባቸው ተግባራትና ስልቶች በዝርዝር አብሮ ማቀድ፤ ቀጥሎ ባለው ሳጥን የተቀመጠው ምሳሌ ተከትለው ማቀድ ይችላሉ፡፡

☛የተዘጋጀውን ዕቅድ ለህብረተሰቡና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ያደርጋሉ/ኦሬንቴሽን ይሠጣሉ፡፡

**ምሳሌ፡-** የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛዋ በዓመቱ በቀበሌዋ ላሉት ነፍሰ ጡር እናቶች መቶ በመቶ  የቅድመ ወሊድ አገልግሎት መስጠት የሚል ግብ ይዛ ከሆነ መከናወን ያለባቸውን ተግባራት በሳምንትና በወር እንደሚከተለው በመሸንሸን ማከናወን ይኖርባታል፡-

✓በቀበሌዋ የሚኖሩትን ነፍሰጡር እናቶች የልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስሮችን በመጠቀም በየሳምንቱ  በሚኖረው የ1ለ5 ትስስር እና በየ15 ቀኑ በሚደረገው የልማት ቡድን ውይይት ወቅት ለይተው እንዲያሳውቋት ግንዛቤ መፍጠር፡፡

✓የቤተሰብ ውይይት ማመቻቸት፣ተፅእኖ ከሚፈጥሩ የነፍሰጡሯ የቤተሰብ አባላት (ባል፣ አማት፣ ጎረቤቶች፣ የሀይማኖት መሪዎች ወዘተ.) ጋር በነፍሰጡሯ ቤት እንዲገኙ በማድረግ ስለ አገልግሎቱ ጥቅምና ምንነት፣ የእነርሱን ✓ድጋፍ በተመለከተ መወያየትና ስምምነት ላይ መድረስ፣

✓በቀበሌው ያሉት የልምድ አዋላጆች  ሁሉም ነፍሰጡር እናቶች የቅመ ወሊድ ምክር እና ምርመራ እንዲያገኙ ወደ ጤና ተቋም እንዲልኩ ግንዛቤ ማስጨበጥ

✓በየወሩ የነፍሰጡር ሴቶች ኮንፈረንስ ማዘጋጀት እና ሌሎች አጋዥ የሚሆኑ ተግባራትን በማቀድ መተግበር፡፡

✓ለቅድመ ወሊድ ክትትል መሰረታዊ የሆኑ ግብዓቶች ሳይቆራረጥ እንዲሟሉ ክትትል ማድረግ፤

ከላይ የተቀመጠው ምሳሌ ሌሎች ፓኬጆችንም በተመሳሳይ መልኩ ታቅደው እንዲተገበሩ የሚያሳይ ነው፡፡ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎችም ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በዚህ መልኩ በማቀድ እንዲተገባሩ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## ለ. የጤና መረጃ ሥርዓትን ማጠናከር

የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መረጃ ስርዓትን በመጠቀም ተደራሽና ጥራት ያለው መረጃ እንዲኖርና ለውሳኔ መጠቀም እንዲቻል ለማድረግ በየደረጃው ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ለመስጠት በማስቻል ረገድ አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሚከናወኑ ተግባራትና የሚሰጡ አገልግሎቶች በተገቢው አኳኋን መመዝገባቸውን፣ መያዛቸውን እና ለሚመለከተው አካል በአግባቡና በወቅቱ መተላለፋቸውን እንዲሁም ለሚፈለገው የአገልግሎት ማጠናከሪያ ና ማሻሻያ እንዲውሉ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የሚከተሉትን ተግባራት ላይ ድጋፍ ያደርጋሉ፡-

### መረጃን መመዝገብ(Recording)

☛የቀበሌውን ህዝብ የጤና ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በቤተሰብ ማህደር መመዝገብ እና በየጊዜው ወቅታዊ እንድታደርግ እንዲሁም ከሌሎች የመረጃ መዝገቦች ጋር የተናበበ እንዲሆኑ መደገፍና መከታተል፣

☛በጤና ኬላው የሚሰጡ አገልግሎቶችን መረጃ አያያዝ ለማሻሻል በእያንዳንዱ ፓኬጅ ላይ የተሟላ መረጃ በአግባቡ እንዲመዘገቡ መደገፍ፣

☛በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ ለሚተገበሩ ፓኬጆች መረጃ የልማት ቡድኖችን ክንዋኔ በማካተት እየተቀበለች በተገቢው መዝገብ መመዝገቧን ማረጋገጥና መደገፍ፣

### መረጃን ማጠናቀር፣ መተንተንና መጠቀም

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የጤና ኬላውን መረጃ በማጠናቀር፣ በመተንተንና ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ አቅማቸውን ለማሳደግ የጤና ጣቢያው ባለሙያ በሚከተሉት ተግባራት ላይ ድጋፍ ያደርጋሉ፡-

☛በጤና ኬላው ግድግዳ ላይ መለጠፍ ያለባቸውን መሠረታዊ መረጃዎች (የፕሮግራም ዕቅድና አፈፃፀም፣ የወባ መከታተያ ቻርት/በወባማ አካባቢዎች/፣ የክትባት መከታተያ ቻርት፣ የማህበረሰብ አቀፍ የጨቅላ ህፃናት ክብካቤ መከታታያ ቻርት/Communitry based newborn

care (CBNC) key indicators monitoring chart/፣ የቀበሌው ፕሮፋይል፣ የቀበሌው ካርታ፣ ወቅታዊ እንዲሆን መደገፍ፣

☛የጤና ኬላውን የፕሮግራሞች/ፓኬጆች/ አፈፃፀም ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር በመሆን መተንተን፣ መተርጎምና ዝቅተኛ አፈፃጸም ባላቸው ፓኬጆች ላይ በማተኮር የችግሮቹን ስርወ-ምክንያት (root cause) በመለየት የመፍትሔ እርምጃዎችን ማስቀመጥና ትግበራውንም መከታተል፣

☛በየ15 ቀኑ ወይም በየወሩ ከልማት ቡድኖች ጋር የሚደረገው ስብሰባ መረጃን መሠረት ያደረገ እንዲሆንና መረጃዎቹን በመተንተን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በጋራ እየለዩ ለአፈፃፀም መሻሻል እንዲጠቀሙበት መደገፍ፣

## የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀትና ለሚመለከተዉ አካል ማስተላለፍ

☛ወደ ጤና ጣቢያ የሚላኩ የጤና ኬላው ሪፖርቶች ተዓማኒነታቸውን፣ወቅታዊነታቸውን፣ እና ሙሉእነታቸውን በመፈተሽ ክፍተት ባለባቸው ላይ ድጋፍ ማድረግና ግብረመልስ መስጠት፣

☛ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሶስት ወርና ዓመታዊ ሪፖርቶች ተዘጋጅተው በወቅቱ ለሚመለከተው ክፍል መላካቸውን ማረጋገጥ፤

☛የበሽታዎች ቅኝትና ምላሽ ሳምንታዊ ሪፖርት እንዲሁም ወዲያዉኑ ሪፖርት መደረግ ያለባቸውን በሽታዎች/ Immediately reported diseases/ ለሚመለከተው ክፍል መላኩን ማረጋገጥ፤

## ሐ. የግብአት አቅርቦት፣ አያያዝና አጠቃቀም

ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ግብዓቶች፣ መድሃኒቶች እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች በወቅቱ በሚፈለገው መጠንና ዓይነት ለፕሮግራሙ ማቅረብ

ያስፈልጋል። በጤና ኬላዎች ላይ ጠንካራ የግብዓት አቅርቦት፣ አያያዝና አጠቃቀም እንዲኖር የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የሚከተሉትን ተግባራት በድጋፍና ክትትል ወቅት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡-

☛በዓመታዊ የዕቅድ ዝግጅት ወቅት ጤና ጣቢያዎች በስራቸው ያሉትን ጤና ኬላዎች ታሳቢ ባደረገ መልኩ የግብዓት ትንበያ በማድረግ በወቅቱ ግዢ መፈፀም፣

☛ለስራ የሚያስፈልጉ ግብአቶች በሚፈለገው ጊዜ፣ ዓይነትና መጠን እንዲኖሩ ድጋፍ መስጠት እና የግብዓት መጠየቂያ ቅጾችን አጠቃቀም ማሳየት እንዲሁም የሚፈለገዉ ግብዓት ለጤና ኬላ መድረሱን እና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣

☛የቢን ካርድ እና HPMRR form (Health Post Monthly Reporting and Re supply) አጠቃቀምና የግብአት ፍላጎት ማስላት ላይ ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣

☛የግብአት አቅርቦት ክፍተት በሚስተዋልባቸው ላይ ህብረተሰቡን በማሳተፍና በማስተባበር የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የጉልበት ድጋፍ እንዲገኝ እገዛ ማድረግ፣

☛በጤና ጣቢያው ስር ባሉት ጤና ኬላዎች ሚዛናዊ ያልሆነ የግብዓት ክምችት በሚኖርበት ጊዜ ጤና ጣቢያው ትርፍ ካለበት ጤና ኬላ እጥረት ወዳለበት ጤና ኬላ በመውሰድ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥና የመድሀኒቶችም የመጠቀሚያ ጊዜ ሳያልፍ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ድጋፍ ማድረግ፤

☛የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን መድሃኒቶች በአገሪቱ መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ ማስተባበር፤

## መ. የሕሙማን ቅብብሎሽ ሥርዓትን ማጠናከር

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በጤና ኬላ ደረጃ አገልግሎት ማግኘት የሚችሉትን ህሙማን አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ተጨማሪ ምርመራና ህክምና የሚያስፈለጋቸውንና ወደ ከፍተኛ ጤና ተቋማት መላክ የሚገባቸውን ተገልጋዮች ከተሟላ መረጃ ጋር በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል። ወደ ከፍተኛ ጤና ተቋማት የተላኩ ህሙማን ያገኙትን አገልግሎትና የሚያስፈልጋቸዉን ክትትል በሚያሳይ መልኩ ለጤና ኬላው ግብረመልስ መድረሱን መከታተል ያስፈልጋል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በሚከተሉት ተግባራት ላይ ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፡-

☛ህሙማን ወይም ተገልጋዮች ወደሚቀጥለው የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም ሂደው ለመጠቀም ያሉትን ምቹና አደናቃፊ ሁኔታዎችን ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ለይተው መፍታት እንዲችሉ ድጋፍ መስጠት፣

✓**ለምሳሌ፡-** አምቡላንስ ወደየ ጎጡ የሚገባበትን ሁኔታ ከማመቻቸት፣ አምቡላንስ በማይደርሱባቸው ጎጦች ባህላዊ የመጓጓዣ ቁሳቁስና የሰው ሀይል ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ፣ የቅብብሎሽ ቅፅ ሞልቶ መላክ፣ ታማሚውን አጅቦ የሚሄድ ሰው መኖሩን ማረጋገጥ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን እንዲተገበሩ መደገፍ፡፡

☛ግብረመልስ በወቅቱና ለጤና ኬላው መሰጠቱን ማረጋገጥ፡፡

## 4.1.2. በፕሮግራሞች አተገባበር ላይ ድጋፍ መስጠት

## 4.1.2.1. የጤና ልማት ሠራዊት ግንባታን ማጠናከር

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ከተዘረጋበት ጊዜ አንስቶ ሞዴል ቤተሰቦችን ማፍራት እንደአንድ ቁልፍ የፕሮግራሙ ግብ ሆኖ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ የሞዴልነት አድማሱንም ከቤተሰብ ወደ ቀበሌ፣ ጤና ጣቢያ እንዲሁም ወረዳ የማስፋት ስራ ይሰራል፤ ይህም እውን የሚሆነው በተደራጀ የልማት ሠራዊት እንቅስቃሴ ሲታጀብ ነው፡፡ በገጠር ያለውን ሴቶችን ማእከል ያደረገ የጤና ልማት ሠራዊት ግንባታ ማጠናከር የአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ቁልፍ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ድጋፍ ይሰጣሉ፡-

☛የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ለልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስር መሪዎች የክህሎት ክፍተታቸውን እየለዩ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሰጡ መከታተልና በስልጠናው ወቅት ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣

☛በሴቶች ልማት ቡድንና አንድ ለአምስት አደረጃጀትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ያሉ ማነቆዎችን ነቅሶ ማውጣት /በማጥናት/ እና ከሚመለከታቸው የአመራር አካላት ጋር በመቀናጀት ለመፍታት ድጋፍ ማድረግ፣

☛በልማት ቡድንና በጤና ኬላ ደረጃ በሚካሄዱ የጤና ልማት ሰራዊት ውይይቶች ላይ በመገኘት በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ አተገባባር ላይ ያሉ ማነቆዎችን በመለየት ከቀበሌ አመራር ጋር በጋራ መፍታት፣

☛ለሴቶች ልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስር መሪዎች በሚሰጠው የደረጃ አንድና ሁለት ስልጠና ላይ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣ መከታተል፤

☛የልማት ቡድን፣ የ1ለ5 ትስስር መሪዎችና አባላት በመመሪያው መሠረት ደረጃ እየተሰጣቸው እና ዝቅተኛ አፈጻጸም ላላቸው ትኩረት ያለው ድጋፍ እንዲሰጣቸው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

☛በልማት ቡድን ደረጃ አመርቂ ውጤት ያስመዘገቡትን በመለየት የእነሱን ተሞክሮ በመቀመር የልምድ ልውውጥ ስራ እንዲሰራ ድጋፍ መስጠት፣

☛በቀበሌ ደረጃ የተሻለ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ልማት ቡድኖች/የ1ለ5 ትስስሮች የእውቅናና ማበረታቻ ስነ-ስርዓት እንዲኖር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣

☛ቀበሌዎች ሞዴል እንዲሆኑ በተዘረጋው አሰራር መሠረት መደገፍ እንዲሁም ሞዴልነታቸው ሲረጋገጥ እውቅና እንዲሰጣቸው የማስተባበርና የመደገፍ ስራ መስራት፣

☛የነፍሰጡር እናቶች ኮንፈረንስ በየወሩ ጊዜውን ጠብቆ እየተከናወነ መሆኑን መከታተል፣ በየኮንፈረንሱ ቃለ-ጉባኤዎች መያዛቸውን መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

ስለሆነም ሴቶችን ማዕከል ያደረገውን የጤና ልማት ሠራዊት ግንባታ ሂደት በማጠናከር ሞዴል ቤተሰቦችን የማፍራት አድማሱ ወደ ሞዴል ቀበሌዎች መፍጠር እንዲሸጋገር ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ማስታወሻ፡-** የመረጃ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ በመደበኛነት ድጋፍ ከሚሰጠው ባለሙያ አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ የጤና ጣቢያውን የጤና መረጃ ስርዓት ቴክኒሻን/HIT/ ሙያዊ ድጋፍ እንዲሰጥ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ ጤና ኬላ ውስጥ ያለው የክትባት መረጃ አያያዝ፣ የክትባት መከታተያ ቻርት አዘገጃጀትና አጠቃቀም ክፍተት ቢኖረው በክትባት ላይ የሰለጠነውን የጤና ጣቢያ ባለሙያ እንዲሄድና ልዩ ድጋፍ እንዲሰጥ ማድረግ ይገባል፡፡

## የሞዴል ቀበሌ ማፍሪያ ሂደት ላይ መደገፍ

### ሀ) የዝግጅት ምዕራፍ

ሞዴል ቀበሌ ለማፍራት ቁልፉ ተግባር የሴቶች የልማት ሰራዊት አደረጃጀትንና አፈጻጸም ይበልጥ ማጠናከር ነው፡፡ በዚህም ሂደት መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና ለማስፋት ዝግጁ ማድረግ እና ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸውን መለየትና ማጠናከር ይገባል፡፡ ይህም ሲባል በልማት ቡድን ና 1ለ5 ትስስር ያልተደራጁ ሴቶች ካሉ ሁሉም እንዲደራጁ ማድረግ፣ ተደራጅተው ወደ ስራ ያልገቡትንም ወደ ስራ የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ለምሳሌ የሴቶች የልማት ሰራዊት አመራሮችን (የ1ለ5ና የልማት ቡድን መሪዎች) አፈጻጸማቸውንና ተነሳሽነታቸውን መገምገምና የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ እንዲሁም የኮማንድ ፖስት አደረጃጀትና የክትትል ስርዓቱን በመፈተሽ ማስተካከልን ያካትታል፡፡ ስለሆነም የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የቅድመ ዝግጅት ተግባራት ላይ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡-

☛የቀበሌው አመራር የቀበሌ ምክር ቤት አባላትንና ለልማት ቡድን አመራሮች በሞዴል ቀበሌ ምንነትና የማስፈፀሚያ ስልቶች ላይ ውይይት በማካሄድ ቀበሌውን ሞዴል ለማድረግ መግባባት ላይ መድረስና የድርጊት መርኃ ግብር እንዲያወጡ ድጋፍ ማድረግ፡፡

☛ከድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት በኂላ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከልማት ቡድንና 1ለ5 መሪዎች ጋር በመሆን የቀበሌውን አጠቃላይ የጤና መረጃ በመሰብሰብ ጥሬ ሀቅን በቤተሰብ ጤና ማህደር ላይ ወቅታዊ እንዲያደርጉ መደገፍ፡፡

☛በተሰበሰበው መረጃ መሰረትም ቀበሌውን ሞዴል ለማድረግ የሚያስችል ግልፅና ዝርዝር ዕቅድ በማዘጋጀት ረገድ ድጋፍ ማድረግ፣

☛ዕቅዱን በቀበሌ ኮማንድ ፖስት በማፅደቅ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ ቀበሌው ህዝባዊ የጤና ኮንፈረንስ እንዲያዘጋጅና ቀበሌው በጤና አፈፃፀም ያለበትን ደረጃ በተመለከተ መተማመን ላይ እንዲደረስ መደገፍ፣ አፈጻጸሙን መሰረት አድርጎ የተሰጠውን ደረጃ የሚገልፅ ባንዲራ (ይህም ዝቅተኛ አፈፃፀም ላለው ቀይ ቀለም ፣መካከለኛ አፈፃፀም ላለው ቢጫ ቀለምና ከፍተኛ አፈፃፀም ላለው አረንጓዴ ቀለም ያለው ባንዲራ) ህብረተሰቡ ሊያየው በሚችል ቦታ በመስቀል ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባት ያስፈልጋል፡፡

## 4.1.2.2. የቤተሰብ ጤና አገልግሎት

በቤተሰብ ጤና አገልግሎት ስር የእናቶችና የጨቅላ ህፃናት ጤና፣ የህፃናት ጤና፣ የቤተሰብ ዕቅድና የወጣቶች ጤና፣ ክትባትና የስርዓተ ምግብ ፓኬጆች የተካተቱ ሲሆን የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከጤና ጣቢያ ባለሙያዎችና ከልማት ቡድኖች ጋር በመሆን በመደበኛነት ለፓኬጆቹ ተግባራዊነት ይሠራሉ፡፡ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ዋና ሚና በፓኬጆቹ ትግበራ ላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የልማት ቡድን/ 1ለ5 ትስስር መሪዎችን አቅም (የሙያ ድጋፍ፣ የግብአት አቅርቦት፣ የአሰራር ስርአት ወዘተ.) መገንባትና ክትትል ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ዋና ዋና ተግባራት የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የልማት ቡድን/ 1ለ5 ትስስር መሪዎች ድጋፍ የሚያደርጉባቸው ናቸው፡-

### ሀ. የነፍሰ-ጡር እናቶች ለይቶ መመዝገብ

የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ነፍሰጡር እናቶችን ለይቶ ለመመዝገብ እንዲችሉ ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋሉ፡-

♣የልማት ቡድን መሪዎች በየትስስራቸው ውስጥ ያሉትን ነፍሰጡር እናቶች በወቅቱና በመደበኛነት በመለየት አስፈላጊውን ምክር በመስጠት ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ማሳወቅ እንዲችሉ የቤተሰብ ጤና መመሪያና ሌሎች እንደ ልማት ቡድን ካርታ ያሉ የስራ መርጃ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ አቅማቸውን መገንባት፤

♣የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከልማት ቡድንና 1ለ5 ትስስር ጋር በመሆን እንደየአካባቢው ባህል ነፍሰጡር የሆኑ እናቶችን የሚለዩበት ዘዴ እንዲያውቁ ድጋፍ ማድረግ፤

♣ነፍሰጡር እናቶች የሚወልዱበትን ቀን ማስላት እና አመዘጋገብ ላይ ድጋፍ ማድረግ፤

## ለ. የነፍሰ-ጡር እናቶች ኮንፈረንስ ላይ ድጋፍ ማድረግ

የነፍሰጡር እናቶች ኮንፈረንስ በሰለጠነ ባለሙያ የሚሰጠውን የወሊድ አገልግሎት ሽፋን እንዲጨምር አይነተኛ ሚና የሚጫወት ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር በመሆን ኮንፈረንሱን ማዘጋጀትና መምራት፣ ነፍሰ-ጡር እናቶች ተገቢውን መልዕክት እንዲያገኙና ተሞክሮዎቻቸውን እንዲለዋወጡ ዋና የዕቅዳቸው አካል በማድረግ አበክረው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ የነፍሰ-ጡር እናቶች ኮንፈረንስ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት የሚከናወን ሆኖ በኮንፈረንሱ ላይ ነፍሰጡር እናቶች ብቻ ሳይሆኑ እንደአስፈላጊነቱ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለምሳሌ ባሎች፣ አማቶች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የልምድ አዋላጆች፣ ከዚህ በፊት በጤና ጣቢያ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች፣ የልማት ቡድንና የ1ለ5 መሪዎችና ወዘተ እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ጤና ኬላውን የሚደግፉ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የነፍሰ-ጡር እናቶች ኮንፈረንስ ለማጠናከር በሚሰሩበት ጊዜ ሊተገብሯቸው የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

☛በየወሩ በሚካሄዱ የነፍሰጡር እናቶች ኮንፈረንስ ላይ በየቀበሌ በመገኘት ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ድጋፍ ለመስጠት የተመደቡ ሚድዋይፍ ወይም በጤና ጣቢያው ሚድዋይፍ የሌሉ ከሆነ ሌሎች ባለሙያዎች በውይይቱ ወቅት ተገኝተው ሙያዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግ፣

☛በውይይቱ ላይ ነፍሰጡር እናቶች እና ሌሎች የተጋበዙ ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች እና አስተያየቶችን በአግባቡ መመለስና በማሳመን የሚፈለገውን አመለካከት እንዲጨብጡ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣

☛በጤና ተቋማት ከሚሰጠው የወሊድ አገልገሎት ጋር በተያያዘ ከህብረተሰቡ አብዛኛውን ጊዜ የሚነሱ ቅሬታዎች ወይም እይታዎች/ perceptions/ በመለየት በጤና ጣቢያ ደረጃ ውይይት በማድረግ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን በማስቀመጥ አስቀድሞ መዘጋጀት፣ በኮንፈረንሱ

ወቅት የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መፍታት ለምሳሌ ነፍሰጡሮቹ ወደ ጤና ተቋማት መጥተው እንዲመለከቱ በመጋበዝ፣ በጤና ተቋም የወለዱ እናቶች ተሞክሯቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ፤

## ለ) የትግበራ ምዕራፍ

የሞዴል ቀበሌ ግብ ሁሉንም የቀበሌው ቤተሰብ በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ትግበራ ሞዴል ማድረግ ሲሆን የሞዴል ቤተሰብ ስልጠናውም ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡ በመሆኑም የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባራትን በአግባቡ መፈፀማቸውን መከታተልና መደገፍ ይጠበቅባቸዋል፡-

☛በቤተሰብ የጤና ማህደር (Family Folder) በተሰበሰበው መረጃ መሰረት እያንዳንዱ ቤተሰብ ሞዴል ከመሆን አንፃር የትኛውን የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ እንዳልተገበረ በመለየትና ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና ከቀበሌ ኮማንድ ፖስት ጋር በመሆን በቅድሚያ ለልማት ቡድንና የ1ለ5 መሪዎችን ለማሰልጠንና ለመደገፍ የተዘጋጀውን ማጠቀሻና የቤተሰብ ጤና መመሪያ በመጠቀም ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በስልጠናው ማብቂያ ወቅትም በልማት ቡድንና በ1 ለ 5 ትስስር ውስጥ ያሉ ሁሉም ቤተሰቦች ሞዴል እንዲሆኑ እና የልማት ቡድኑም ሞዴል እንዲሆን ለማድረግ የየልማት ቡድናቸውንና የትስስራቸውን በተገኘው መረጃ መሰረት ዕቅድ እንዲያዘጋጁ መደገፍ፡፡

በተዋረድም የልማት ቡድን አመራሮች በልማት ቡድናቸው ጥልቅ ውይይት በማድረግ ሁሉም የልማት ቡድን አባላት ሞዴል እንዲሆኑ ለማድረግ የቤተሰብና የትስሰር ዕቅድ ያዘጋጃሉ፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ በዕቅዱ መሰረት እየሰራ መሆኑን የልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስር መሪዎች ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው በሚካሄደው የልማት ቡድን ውይይት ወቅት የልማት ቡድኑን ዕቅድ አፈፃፀም በመገምገም የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል፡፡

በተመሳሳይም የቀበሌው ኮማንድ ፖስት ለልማት ቡድንና ለ1ለ5 መሪዎች እንደየአካባቢው ሁኔታ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ተከታታይ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

በልማት ቡድኖች መካከል በጎ የውድድር መንፈስ እንዲፈጠርና የሞዴል ቤተሰብ የማፍራት ስራውን ለማቀላጠፍ በልማት ቡድኖች መካከል የልምምድ ልውውጥ በማድረግ ጥሩ አፈፃፀም ያላቸው የልማት ቡድኖች ለሌሎች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባል፡፡

በቀበሌ ደረጃ እንደማህበረሰብ መሰራት ያለባቸው ስራዎች ለምሳሌ በማህበራዊ ተቋማት እና በሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች የጋራ መፀዳጃ ቤት ግንባታ፣ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ትግበራ፣ ትምህርት ቤቶችን በጤና ሞዴል ማድረግና ቀበሌውን ከቤት ውስጥ መውለድ ነፃ ማድረግ፣ ቀበሌውን ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነፃ ለማድረግ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ዕቅዶች በማዘጋጀት በኮማንድ ፖስት እየተመራና አፈፃፀሙም እየታየ መተግበር ይኖርበታል፡፡

☛በየኮንፈረንሱ ቀናት ውይይት የሚደረግበት ነጥብ ላይ በደንብ መዘጋጀትና አጋዥ የሆኑ መመሪያዎችን/መፅሐፍቶችን መጠቀም (ለምሳሌ፡ የቤተሰብ ጤና መመሪያ፣ የነፍሰጡር እናቶች ኮንፈረንስ ማካሄጃ ሰነድ፣ የነፍሰጡር እናቶች መቆያ ክፍል በተመለከተ የተዘጋጀውን ሰነድ እና የመሳሰሉት)፣

☛በኮንፈረንሱ ወቅት ከወሊድ ጋር ተያይዞ ከተሳታፊዎች ለሚነሱ ጉዳዮች ተገቢውን ምላሽ መስጠትና ከአቅም በላይ የሆኑትን በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ለችግሩ መፍትሔ የሚገኝበትን መንገድ በመፈለግ ማገዝ፣

☛ለኮንፈረንሱ መካሄድ የሚያስፈልጉ መርጃ መሳርያዎችንና ግብዓቶች እንዲኖሩ አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣

☛ይህ ዓይነት ኮንፈረንስ ለነፍሰጡር እናቶች ብቻ የሚዘጋጅ ሳይሆን ከወለዱም በኂላ ቀጣይነት ባለው መልኩ ስለጨቅላ ህጻናት ክብካቤ፣ ☛በእርግዝናና በወሊድ ወቅት የሚከሰቱ አደገኛ ምልክቶች፣ ስለድህረ ወሊድ አገልግሎት ጥቅም፣ በጡት ማጥባት፣ በተጨማሪ ምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ ላይ በማተኮር የእናቶችና የህፃናትንና ጤናና እድገት ሊያሻሽል እንዲያስችል ሆኖ መቀጠል አለበት፡፡

## ሐ. ተኮር የቅድመ-ወሊድ አገልግሎት አሠጣጥ ላይ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በጤና ኬላ ደረጃ የቅድመ ወሊድ አገልግሎት ለመስጠት ከነፍሰጡር እናቶች ጋር ቀጠሮ በሚኖራቸው ጊዜ የጤና ጣቢያ ሚድዋይፍ ነርስ፣ ጤና መኮንን ወይም ሌሎች ነርሶች ወደ ጤና ኬላ በመሄድ ተኮር የቅድመ ወሊድ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሙያ ድጋፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ላይ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡-

♣የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለባቸውን የዕውቀትና የክህሎት ክፍተቶችን መለየት፤

♣የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት በአካል በመገኘትና ቼክሊስት በመያዝ መከታተልና በተግባር ማሳየት፤

♣ለተኮር ቅድመ ወሊድ ክትትል የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በበቂ ዓይነትና መጠን መኖራቸውን ማረጋገጥና ክፍተት በሚኖርበት ጊዜ እንዲሟሉ ማድረግ፤

♣በጤና ኬላ ደረጃ ለማይሰጡ የተኮር ቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎቶች ወደ ቀጣይ ጤና ተቋም እንዲልኩ እንዲሁም ነፍሰጡር እናቶች እርጉዝ መሆናቸውን እንዳወቁ በተቻለ መጠን የመጀመሪያውን ክትትል በጤና ጣቢያ እንዲያደርጉ ግንዛቤ ማስጨበጥና አፈጻጸሙን በጋራ መከታተል፤

## መ. የወሊድ አገልግሎት ላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን አቅም መገንባት

የወሊድ አገልግሎት በሰለጠነ ባለሙያ በጤና ጣቢያ የሚሰጥ በመሆኑ ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ምጥ የጀመራቸውን እናቶች መረጃ ከልማት ቡድንና ከ1ለ5 መሪዎች እንዳገኙ ወዲያው ለጤና ጣቢያ በማሳወቅ አምቡላንስ እንዲላክ ማድረግ ያስፈልጋል። እንደ አስፈላጊነቱም የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች መንገድ ላይ ድጋፍ ለመስጠት ምጥ ከጀመራቸው እናቶች ጋር ወደ ጤና ጣቢያ አብረው ሲሄዱ ድንገተኛ ክስተት ቢያጋጥም ምን ዓይነት ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው እውቀትና ክህሎት መፍጠር ያስፈልጋል። ከርቀትና ከመልክዓምድር አቀማመጥ ጋር ተያይዞ ለትራንስፖርት አመቺ በማይሆንባቸው ቦታዎች እና የእርግዝናው ሁኔታ የጤና ባለሙያ የቅርብ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ከሆነ በእናቶች ማቆያ ክፍል እንዲቆዩ እናቶችን ለይተው እንዲልኩ ማስተማርና ማበረታታት። አምቡላንስ በምትዘገይበት ወይም በሌላ ምክንያት ምጥ የያዛት እናት ቤት ውስጥ ለመውለድ የሚያስገድድ ሁኔታ ቢፈጠር የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የማዋለድ አገልግሎት ለመስጠት እንዲዘጋጁ ማብቃት ያስፈልጋል።

## ሠ. ድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ማጠናከር

ሁሉም በጤና ጣቢያ የወሊድ አገልገሎት ያገኙ እናቶች በጤና ጣቢያው ለ24 ሰዓት በማቆየት የመጀመሪያውን የድህረ ወሊድ አገልግሎት ወደ ቤታቸው ከመመለሳቸው በፊት ማግኘት አለባቸው። ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ከጤና ተቋማት ውጪ ከወለዱ በ24 ሰዓት ውስጥ የቤት ለቤት የድህረ ወሊድ አገልግሎት መስጠት ያስፈልጋል። ከዚያ በኃላ ሁሉም እናቶች በ3ተኛ ቀን እና 7ኛ ቀን በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የቤት ለቤት የድህረ ወሊድ አገልግሎት እንዲሰጡ መከታተልና መደገፍ ያስፈልጋል። በመሆኑም ሁሉም እናቶች በወቅቱ የድህረ ወሊድ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከጤና ጣቢያና ከልማት ቡድን መሪዎች መረጃ በፍጥነት እንዲያገኙ መደረግ አለበት። በመሆኑም የጤና ጣቢያ

ባለሙያዎች በጤና ኬላ የሚሰጠውን የድህረ ወሊድ አገልግሎት ለማጠናከር በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ድጋፍ ያደርጋሉ፡-

ቆየጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያላቸውን የአመለካከት፣ እውቀትና የክህሎት ክፍተት መለየት፤

ቆየጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት በአካል በመገኘትና ቼክሊስት በመያዝ መከታተልና በተግባር ማሳየት፤

ቆለድህረ ወሊድ ክትትል የሚያስፈልጉ በበቂ ዓይነትና መጠን ግብዓቶች መኖራቸውን ማረጋገጥና ክፍተት በሚኖርበት ጊዜ እንዲሟሉ ማድረግ፤

ቆበጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የሚሰጠው የድህረ ወሊድ አገልግሎት ለእናትዬዋና ለጨቅላው ህጻን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት መሆኑንና በቤተሰብ ማህደር ላይ በአግባቡ መመዝገቡን መከታተልና መደገፍ ያስፈልጋል፡፡

ቆበድህረ ወሊድ ጊዜ በእናትየዋ እንዲሁም በጨቅላ ህጻኑ ላይ ሊከሰቱ ስለሚችሉ አደገኛ ምልክቶች ማስተማርና አስፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፡፡

## ረ. የክትባት አገልግሎትን ማጠናከር

ጤና ኬላው በቀበሌው የክትባት አገልግሎት ለማጠናከር አገልግሎቱን በመደበኛነት በውሎ-ገብና በቋሚ ጣቢያ እንዲሁም በዘመቻ መልክ ይሰጣል፡፡ በአገራችን የሚሰጠው የክትባት አገልግሎት ለህፃናትና በመውለድ ዕድሜ ክልል ለሚገኙ ሴቶች ሲሆን የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሚሰጡት የክትባት አገልግሎት ጥራቱን የጠበቀና ተደራሽ እንዲሆን ለድጋፍ የሚሰማሩ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡-

ቆበክትባት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያሉ የአፈፃፀም ክፍተቶችን በዝርዝር መዳሰስና ክፍተቶቹን በፈርጅ በፈርጅ መከፋፈል ያስፈልጋል፤

ቆየተገኘው ክፍተት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የክህሎት ክፍተት ከሆነ የክትባት አገልግሎቱ የሚሰጡባቸውን ቀናት መለየትና የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ክትባቱን በፕሮቶኮሉ መሰረት እየሰጡ ስለመሆኑ የክትባት መዛግብት በመፈተሽ፣ በምልከታና መጠይቅ በማድረግ በአገልግሎት አሰጣጡ የሚስተዋሉ ክፍተቶች ላይ ሰርቶ በማሳየት ማብቃት፤

ቆሳይቆራረጥ የክትባት አገልግሎት እንዲሰጥ ለጤና ኬላዎች በመደበኛነት ክትባትና የክትባት መስጫ ቁሳቁሶች አቅርቦት እንዲኖር ድጋፍ ማድረግ፣

ቆድጋፉ የክትባት መከታተያ ቻርት አዘገጃጀትና አተናተን፣ ክትባት ያቋረጡ ህፃናት በማፈላለግ እንዲጨርሱ ማድረግ፣ የክትባት ቅዝቃዜ ሰንሰለት አጠባበቅ፣ የክትባትና የክትባት አሰጣጥ

ደንብ (VVM Policy)፣ የክትባት መድኃኒት ብክነት ቅነሳ፣ ከክትባት በኃላ በተገቢ የቆሻሻ አወጋገድና ከክትባት ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ቀላልና ከባድ የጎንዮሽ ጉዳቶች መለየትና ወደ ቀጣይ ጤና ተቋም መላክ፤ እንዲሁም የኩፍኝ፣ የጨቅላ ህጻናት  የመንጋጋ ቆልፍ በሽታዎች ቅኝትና ምላሽ ላይ ድጋፍ ማድረግን ይጨምራል፡፡

## ሰ. የህፃናት እድገት ክትትልን ማጠናከር

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የህጻናት እድገት ክትትል በየጊዜው እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ይህንን የህጻናት የእድገት ሁኔታ መረጃ በማጠናቀርና በመተንተን የማህበረሰብ ውይይት በማድረግ የአመጋገብ ስርአትን በተመለከተ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን በመለየት በመደበኛነት ከልማት ቡድን መሪዎች ጋር በመሆን ውይይቶችን ያመቻቻሉ፡፡ ይህንን ውጤታማ ለማድረግ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ድጋፍ መስጠት አለባቸው፡-

☛የህጻናት ክብደት አወሳሰድ፣ ቻርት አጠቃቀምና  አመዘጋገብ ላይ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣

☛በልኬት ውጤት መሰረት የህፃናት ክብደት ውጤት በመተንተን ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ክብደት ያላቸውን በመለየት በተቀናጀ የህጻናት  ጤና ህክምናና ክብካቤ ማኑዋል መሰረት አስፈላጊውን ምክርና ክብካቤ እንዲደረግላቸው መደገፍ፣

☛በክብደቱ ውጤት መሰረት ከእናቶችና ከማህበረሰቡ ጋር ውይይቶችን በመምራት ሂደት የችግሩን ምንጭ ለይቶ ማውጣትና የመፍትሄ እርምጃዎች ላይ እንደየአስፈላጊነቱ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ውይይቱ ጤናማ ዕድገት ካላቸው ህፃናት ጋር እየተመሳከረ እየተሰጠ መሆኑን መከታተልና ድጋፍ ማድረግ፤

☛የህፃናት ስርዓተ ምግብን በተመለከተ የምጥን አዘገጃጀትና አመጋገብ ላይ ድጋፍ ማድረግ፤

## ሸ. የታመሙ ጨቅላ ህፃናትና ህጻናት ህክምናና ክብካቤን ማጠናከር

የጨቅላ ህፃናትና የህጻናት ህመምና ሞት ለመቀነስና አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ ማህበረሰብ አቀፍ የተቀናጀ የጨቅላ ህፃናትና የህጻናት ህክምናና ክብካቤ በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እየተሰጠ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ ከፕሮግራሙ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ድጋፍና ክትትል ከፍተኛ መሆን አለበት፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በተለይ፡-

☛ማህበረሰብ አቀፍ የተቀናጀ የጨቅላ ህፃናትና የህጻናት ህክምና ክብካቤ አገልግሎት ላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣

☛ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችና ሌሎች ግብዓቶችን ሳይቆራረጥ ማቅረብ፣

☛ማህበረሰብ አቀፍ የተቀናጀ የጨቅላ ህፃናትና የህጻናት ህክምናና ክብካቤ ላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በቻርት ቡክሌት መሠረት በትክክል መፈተሸዋን፣ መሰየሟንና ህክምናና የምክር አገልግሎት መስጠቷን ወይም ከፍተኛ ህክምና የሚያስፈልጋቸውን ወደ ከፍተኛ ጤና ተቋም መላኳን ባህረ-መዝገቡን በመገምገም መጣረዝ መኖሩንና አለመኖሩን በማረጋገጥ በክፍተቶች ላይ ድጋፍ ማድረግ፤

በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ክፍተት ካለ በህጻናት ጤና ህክምና የሰለጠነ የጤና ጣቢያ ባለሙያ ወደ ጤና ኬላ በመሄድና በጤና ጣቢያም በተግባር ጭምር በማሳየት ድጋፍ መስጠት፤

☛የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ተጠቃሚነት ላይ በየጊዜው ግምገማና የክሊኒካል ሜንተሪንግ ድጋፍ መስጠት፣

በቀበሌው በICCM/CBNC የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ውስንነቶችን በመለየትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በሚፈቱበት ዙሪያ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት መደገፍ፤

## ቀ. የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ማጠናከር

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የተለያዩ የአጭርና የረጂም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶች እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ የዚህን አገልግሎት ጥራት ለማሻሻል የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ በመሆኑም በሚከተሉት ተግባራት ላይ ድጋፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

☛ተጠቃሚዎች በዕውቀትና በምርጫቸው መሰረት የፈለጉትን የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴ እንዲያገኙ ጥራት ያለው የምክክር አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ድጋፍ መስጠት፣

☛የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት አሰጣጥ በተቀመጠው ፕሮቶኮል/መመሪያ መሰረት መሆኑን በማየት ክፍተቶች ካሉ አስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ፣

☛ጤና ኬላው የረጂም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ለአገልግሎቱ የተቀጠሩ እናቶች በሚመጡበት ቀን በአካል በመገኘት የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣

☛በቤተሰብ ዕቅድ ዙሪያ የታዩ የአፈጻጸም ውስንነቶችና መንስኤዎቻቸውን በመፈተሽ በማህበረሰብ ደረጃ መፈታት ያለባቸው ጉዳዮች ላይ ድጋፍ መስጠት፤

☛ጤና ኬላው የረጅም ጊዜ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት (የሉፕ እና የኢምፕላንት የቤተሰብ እቅድ አማራጭ ዘዴዎች) የሚሰጥ ከሆነ ለነዚህ አገልግሎት የሚያግዙ ግብዓቶች የተሟላ

መሆኑን ማረጋገጥና አስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ፣ አገልግሎቱ የማይሰጥ ከሆነ ወደሚቀጥለው የጤና ተቋም እንዲልኩ መደገፍ፤

☛ጤና ኬላው የረጅም ጊዜ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በተመለከተ ሪፖርት መመዝገቢያ ላይ በየዓመቱ የኦዲቲንግ ስራ እንዲሰሩ እገዛ ማድረግ፡፡ የጤና ጣቢያ ባለሙያ ለድጋፍ በሚሰማራበት ጊዜ በጤና ጣቢያ የረጅም ጊዜ የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚ የሆኑ የቀበሌዋን ሴቶች ዝርዝር ይዞላት መሄድ ይኖርበታል፡፡

## 4.1.2.3. በሽታ መከላከልና መቆጣጠርን ማጠናከር

በዚህ ስር የሚጠቃለሉት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች የወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር፣ የቲቢና ስጋ ደዌ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስና የአባላዘር በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር፣ ትኩረት የሚሹ የሀሩር (የትሮፒካል) በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ሲሆኑ ከተጠቀሱት ከዋና ዋናዎቹ በተጨማሪ የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ስራዎች ያከናውናሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህን በሽታዎች በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የሚከተሉት ተግባራት ላይ ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በወባ መከላከልና መቆጣጠር ላይ በተለይም በቤት ውስጥ የፀረ ወባ ኬሚካል ርጭት፣ በፈጣን የወባ መመርመሪያ ኪት አጠቃቀም፣ ህክምና፣ ☛በወባ በሽታ መከታተያ ቻርት አዘገጃጀትና መረጃ አጠቃቀም፣ የወባ መራቢያ ቦታዎች ልየታና ማስወገድ በተለይ Larval identification and larviciding ላይ ድጋፍ መስጠት፣

☛ከጤና ጣቢያ ህክምናቸውን በአቅራቢያቸው እንዲከታተሉ ወደ ጤና ኬላ የተላኩ የቲቢ ህሙማንን መድሃኒታቸውን በአግባቡ እንዲወስዱ ጥብቅ ክትትል ማድረግ፤ የታማሚ ቤተሠቦች ተገቢውን ምርመራና ክትትል አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤ ከመድሀኒት ጋር ቁርኝት (drug Adherence) ምክር አሰጣጥ፣ ህክምና የጀመሩ የቲቢ ህሙማን መድሃኒታቸውን ቢያቋርጡ ከጤና ጣቢያና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን ህሙማኑን በፍጥነት ፈልጎ ማግኘትና ህክምናቸውን እንዲቀጥሉ በማድረግ ረገድ ድጋፍ ማድረግ፤

☛ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ፣ የምክክር አገልግሎት፣ ማግለልና መድሎን በተመለከተ ግንዛቤ መፍጠር፣ ስለ አባላዘር በሽታ መከላከል እና ጥንቃቄ ስለማድረግ እና ህክምና መኖሩን ማስገንዘብ፣ የፀረ-ኤች አይ ቪ መድሃኒት

ጀምረው ያቋረጡ ሰዎች አፈላልጎ ህክምና ማስቀጠል፣ በተጨማሪም እንደአስፈላጊነቱ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተባብሮ ስለመስራት በተመለከተ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣

☛ትኩረት በሚሹ የሀሩር (ትሮፒካል) በሽታዎች መከላከል ላይ እንደየአካባቢው የሚለያይ ቢሆንም በበሽታዎቹ ምልክቶች፣ ህክምና፣ በማህበረሰብ አቀፍ መድሀኒት እደላ፣ በሽታዎቹ በሚያስከትሉት ተፅዕኖ፣ በመከላከያ መንገዶች ላይ ስልጠና መስጠትና መከታተል፣

☛ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠርን በተመለከተ ለበሽታዎቹ ሊያጋልጡ የሚችሉ ሁኔታዎች (ሊስተካከሉ የሚችሉ አጋላጭ ሁኔታዎች እንደ ሲጋራ ማጨስ፣ የአካል እንቅስቃሴ አለማድረግ፣ ያልተስተካከለ አመጋገብ፣ አልኮልና ሌሎች አደንዛዥ እፆች መጠቀምን)፣ የጤና ማበልፀግና የበሽታ መከላከያ መንገዶች ላይ ግንዛቤ መፍጠር ወዘተ ላይ አቅም መገንባትና መከታተል፣ ለስኳር በሽታ፣ የደም ግፊት፣ ካንሰር፣ የመተንፈሻ አካላት በሽታ ወዘተ ያላቸው ሰዎች ልየታና ወደሚቀጥለው የጤና ተቋም መላክ በተመለከተ ድጋፍ ማድረግ፤

## 4.1.2.4. ሀይጂንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ማጠናከር

በዚህ ስር የሚካተቱት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ሰባት ሲሆኑ እነሱም የመጸዳጃ ቤት ግንባታና አጠቃቀም፣ የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ የግልና የአካባቢ ንፅህና፣ የምግብ ንፅህና አጠባበቅ፣ የውሃ ንፅህና አጠባበቅ፣ ቆርጣሚና ተናዳፊ እንስሳት መቆጣጠርና ጤናማ የመኖሪያ ቤት አያያዝ ናቸው፡፡ በመሆኑም የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በሚከተሉት ተግባራት ላይ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡-

☛ህዝብ በብዛት የሚሰበሰብባቸው አካባቢዎች (እንደ ገቢያ ቦታ፣ በእምነት ተቋማት፣ በትምህርት ቤቶች) የሀይጂንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ላይ ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ጋር በመሆን ግንዛቤ መፍጠርና ከእነዚህ አካላት ጋር መስራትና መከታተል፣

☛የግል ንፅህና አጠባበቅ በተመለከተ የአልባሳት ንፅህናና አያያዝ፣ የሰውነት አካላትና የአፍ ንፅህና እንዲሁም ስለምግብና ውሃ ንፅህና አጠባበቅ ላይ ብሎም የፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አመለካከትና እውቀት መፈተሸና በክፍተቶች ላይ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፤

☛የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በእያንዳንዱ ቀበሌ ሊካሄድ የሚታሰቡ የማህበረሰብ መር ጠቅላላ

ሳኒቴሽን ማቀጣጠል ስራዎችን በአመት እቅድ ውስጥ በማካተት የማቀጣጠል ስራውን መምራትና ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣ ቀበሌው ውስጥ ባሉት ቤቶችና ህዝብ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች የተሻሻሉ መፀዳጃ ቤቶች እንዲገነቡና ሜዳ ላይ ከመፀዳደት ነፃ የሆነ ቀበሌ ከመፍጠር አንፃር መደገፍ፡፡ ይህ የማቀጣጠል ስራ በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ማኑዋል መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አምስት

## 5. የስራ አፈጻጸም ግምገማ ማካሄድ /Review Meeting/

### 5.1. በጤና ጣቢያ ደረጃ የሚደረግ ወርሃዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ

በጤና ጣቢያ ደረጃ የሚካሄደው ወርሃዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ ዋና ዓላማን መሰረት ያደረገ እና የሥራ አፈጻጸም ለማሻሻል፣ የልምድ ልውውጥን ለማዳበርና የጤና ኤክስቴንሽንና የጤና ጣቢያ ባላሙያዎችን የስራ ላይ አቅም ለመገንባት ነው፡፡ ይህ ወርሃዊ ግምገማ ሁሉም የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እና የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በተገኙበት ቢያንስ ለአንድ ቀን ይካሄዳል፡፡ ወርሃዊ ግምገማው የሚካሄደው መረጃን መሰረት አድርጎ እንደመሆኑ መጠን ጤና ጣቢያው እና ጤና ኬላዎች የጤና መረጃ ስርዓትን/HMIS/ እንዲሁም የድጋፍና ክትትል ግኝቶችን በተከተለ መልኩ በወርሃዊ ሪፖርታቸው ላይ የተመረጡ መለኪያች ይዘው መቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ወርሃዊ ግምገማው የመነቃቀፊያ ሳይሆን እንደ አሃድ የተገኙት ውጤቶችን በማወደስ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚደረግበት እንዲሁም የተስተዋሉ ክፍተቾችን ደግሞ የጋራ ድክመቶች ናቸው ብሎ በመውሰድና የጋራ ርብርብ በማድረግ ለመቅረፍ የጋራ መፍትሔዎች የሚቀርብበት የመማማሪያና አቅም መገንቢያ መድረክ መሆን ይኖርበታል፡፡ ግምገማው በዋናነት ስራን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን ስራን በማደናቀፍ ላይ ሚና የነበራቸው አመለካከቶችም ከስራው ጋር አብሮ ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቀበሌ ደረጃ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም በቀበሌ ኮማንድ ፖስትም ጭምር መገምገም አለበት፡፡

## በወርሀዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ የሚሳተፉ አካላት

☛የጤና ጣቢያ ዳይሬክተር

☛የጤና ጣቢያና ጤና ኬላ ትስስር አስተባባሪ

☛የአሃዱ ደጋፊ የወረዳ ጤና ጥ/ጽ/ቤት ተወካይ

☛የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የጤና ጣቢያው ባለሙያዎች

☛አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለምሳሌ የቀበሌ ሊቀመንበሮች ወዘተ፡፡

የተሳካና ያልተቆራረጠ ወርሃዊ የስራ አፈፃጸም ግምገማ ለማከናወን የጤና ጣቢያ ዳይክሬተር እና የጤና ጣቢያና ጤና ኬላ ትስስር አስተባባሪው መሰረታዊ የኮሚኒኬሽን፣ የአሳታፊነት፣የዉሳኔ ሰጪነት እና የማነቆዎች መንስኤዎቻቸውንና መፍትሄዎቻቸውን የመለየት፣ ውጤትን የመመዘን ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡

## ለወርሃዊ ግምገማው የሚያስፈልግ ቅድመ ዝግጅት

☛ለወርሃዊ ግምገማው ቀን አስቀድሞ መወሰንና መርሃ ግብሩን ማሳወቅ

☛የስብሰባውን አጀንዳ አስቀድሞ ማዘጋጀት

☛በወርሃዊ ሪፖርት ቅጽ መሰረት ተሞልቶ የሚቀርብ የአፈጻጸም ሪፖርት/ ጤና ኬላዎች እና ጤና ጣቢያው የተለያዩ ክፍሎች አስቀድመው ወርሃዊ አፈጻጸማቸውን ለጤና ጣቢያው ዳይሬክተር ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

☛የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግና የተገኙ ውጤቶች ሪፖርት አጠናቅሮ ማቅረብና ለግምገማው በግብዓትነት መጠቀም፣

## በወርሃዊ ግምገማ ቀን ትኩረት የሚደረግባቸው መስኮች

ሁሉም ቀበሌዎች ሞዴል የሚሆኑበት አጠቃላይ አቅጣጫ በመያዝ በሚከተሉት ቁልፍና አበይት ተግባራት ላይ ትኩረት አድርጎ ውይይት ማድረግ ከፍተኛ አፈፃፀም ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ለመገንባት ያስችላል፡-

☛የሴቶች ልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስር መሪዎች ጋር መስራትን በተመለከተ (የሴቶች ልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስር መሪዎች ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እና ከጤና ጣቢያው ባለሙያዎች ጋር የሚኖራቸው የስልጠና፣ ሞዴል ቤተሰብ ምረቃ፣ የግምገማ እና የምክክር ሁኔታዎች)፣ የአደረጃጀትና የሠራዊት ግንባታው እንቅስቃሴ ያለበት ሁኔታ፤

☛አበይት በሆኑ ተግባራት አፈጻጸም (የእናቶች፣ ጨቅላ ህጻናት እና ህጻናት ጤና አጠባበቅ፣ ስርዓተ-ምግብ፣ የቤተሰብ እቅድ፣ ወባና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች መካላከልና መቆጣጠር፣

የግልና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ የህሙማን እና ወላዶች ቅብብሎሽ፣ የግብዓት አቅርቦት ወዘተ.)

☛ከላይ የተዘረዘሩት ፕሮግራሞች አፈፃፀም ዙሪያ ክፍተት በሚስተዋልባቸው ጉዳዮች ላይ በቀጣይ ለማጠናከር የችግሮቹን ስርወ ምክንያቶች/root cause/ በመተንተን የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀትና ፈፃሚ ባለቤት በማስቀመጥ ተግባራዊነቱንም መከታተል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የተሻለ አፈፃፀም ካለበት ቀበሌ/ቦታ ተሞክሮውን ወደ ሌሎቹ ቀበሌዎች የሚሰፋበት ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

☛ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከጤና ጣቢያው ባለሙያዎች የሚደረግላቸው ድጋፍ ውጤታማነትን መገምገም፣

☛የእውቀት እና ክህሎት ሽግግር (ጤና ጣቢያው የእውቀት ወይንም የክህሎት ክፍተቶችን እየለየ የተለያዩ ስልጠናዎችን የወሰዱ ባለሙያዎችን ወይንም የአጋር አካላት ባለሙያዎችን በመጋበዝ አጫጭር ስልጠናዎች መስጠት ይችላል፡፡)

## የወርሃዊ ግምገማ  አጀንዳ መነሻ ናሙና

## 6.አፈጻጸምን ማዕከል ያደረገ ዕውቅናና ማበረታቻ መስጠት

ጤና ጣቢያዎች በስራቸው የሚገኙ ጤና ኬላዎች/ ቀበሌዎች በየወሩ በሚኖረው የስራ አፈፃፀም ግምገማ መሠረት ጥሩ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን በመለየት መመዝገብና ስኬታቸው ቀጣይነት ያለው መሆኑ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ በመሆኑም እንደየ ጤና ጣቢያው ማኔጅመንት የሚወሰን ቢሆንም በየሩብ ዓመቱ የተለያዩ ማበረታቻዎችን እንዲሁም በየስድስት ወሩ የላቀ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ከጤና ጣቢያ ስራ አመራር ኮሚቴ ጋር በመነጋገር እውቅናና ማበረታቻ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በየስድስት ወሩ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የስራ አፈፃፀም ግምገማ /ሚዛናዊ ስኮር ካርድ/ ማካሄድና ጥሩ አፈፃም ያስመዘገቡትን በተለያዩ የማበረታቻ ስርዓቶች በመዘርጋት ማትጋትና የስራ ተነሳሽነታቸውን ማጎልበት፡፡ ይህም ጥሩ አፈፃፀም ያላቸውን ለይቶ ለማበረታታትና ክፍተት ያለባቸውን ደግሞ ትኩረት ያለው ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል፡፡

### 6.1. ከውጤታማ ድጋፍና ክትትል ከሚያደርግ ጤና ጣቢያ የሚጠበቁ ጠቋሚ መለኪያዎች

☛በአግባቡ የተደራጁና ወደ ተግባር የገቡ የልማት ቡድንና 1ለ5 ትስስሮች፣

☛በቀበሌው የሚኖሩ ሁሉም ቤተሰቦች የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ተግብረው ሞዴል የሆኑበት፣

☛ቀበሌው ቤት ከመውለድ ሙሉ በሙሉ ነፃ የሆነ፣

☛ቀበሌው ሜዳ ላይ ከመፀዳዳት ሙሉ በሙሉ ነፃ የሆነ እና

☛የማህበረሰብ ጤና መድን ሽፋን 100% ሲሆን

☛ሁሉም በቀበሌው ያሉ ትምህርት ቤቶች በጤና ሞዴል ሲሆኑ፤ ይህ ሲባል የሞዴል መመዘኛ መስፈርቱ የት/ት ቤቶችን ደረጃ እና ሊሰጡ የሚገቡ የጤና አገልግሎቶችን ያገናዘበ ሊሆን ይገባዋል፡፡

# 7. አባሪዎች

## 7.1. የድጋፋዊ ክትትል ቼክሊስት

## ይህ ቼክሊስት ለናሙና የቀረበ በመሆኑ እንደየአስፈላጊነቱ እየከለሱ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

***ማስታወሻ፡- በየቀበሌው በመደበኛነት ድጋፍ የሚሰጡ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች የድጋፋቸውን ዝርዝር ተግባራት ለጤና ጣቢያው ዳይሬክተር ማቅረብና ሌላ ጊዜ ሲመለሱ አፈፃፀሙ መሻሻሉን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡***

| ጊዜ | ተግባራት | አቅራቢ | አመቻች |
|---|---|---|---|
| 3:00-3:30 | መክፈቻ እና እንኳን ደህና መጣችሁ | የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ዳይሬክተር | የትስስሩ አስተባባሪ |
| 3:30-3:50 | የጤና ጣቢያው አፈጻጸም ሪፖርት | የቡድን አስተባባሪ | የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ዳይሬክተር |
| 3:50-4:30 | ውይይት | የቡድን አስተባባሪ | |
| 4:30-4:50 | የሻይ እረፍት | | |
| 4:50-6:30 | የጤና ኬላዎች አፈጻጸም ሪፖርት | የጤና ኤክስቴኝሽን ሰራተኞች | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የድጋፋዊ ግብኝት ዉጤቶች/ግኝቶች | የትስስሩ አስተባባሪ | |
| 6:30-7:30 | ምሳ | | |
| 7:30-8:00 | የጤና ጣቢያውን የተለያዩ ክፍሎች የእያተዘዋወሩ መጎብኘት (እንደአስፈላጊነቱ) | የየክፍሉ ተጠሪዎች | የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ዳይሬክተር |
| 8:00-9:00 | ውይይት | የትስስሩ አስተባባሪ | |
| 9:00-10:00 | በተመረጡ ርዕሶች/ፕሮግራሞች ላይ የእውቀት /የክህሎት ስልጠና | ባለሙያዎች | |
| 10:00-10:20 | የሻይ እረፍት | | |
| 10:20-10:50 | የሚቀጥለውን ወር የድርጊት መርሃ ግብር ማውጣት | ተሳታፊዎች | |
| 10:50-11:00 | የግምገማው ማጠቃለያ | የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ ዳይሬክተር | |